# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

መስከረም 22 ቀን 2001 ዓ.ም

## የኦሮሞን ሕዝብ ትግል ለማፈን የሚጎነገነውን ሻጥር እናውግዝ!

የወያኔ አገዛዝ በአንዳንድ የባዕድ ሀገሮች በመረዳት የኦሮሞን ሕዝብ ትግል ለማፈን ከተወሰነ አንጃ ጋር ድርድር በሚል ሽፋን ሕዝብን ትጥቅ ለማስፈታት ላይ ታች እያለ በመሆኑ ኢሕአፓ ይህን ሴራ እያወገዘ ከኢትዮጵያዊው የኦሮሞ ታጋይ ሕዝብ ጎን በመቆም ትግላችን ይቀጥል ሲል ጥሪውን ያስተጋባል።

ኢሕአፓ ከተመሰረተ ከ1964 ዓ.ም. ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የእኩልነት መብት ቆርጦ የታገለ ሲሆን በኦሮሞ ሕዝብ ስም ተደራጀን ብለው ግን አንድም በየጊዜው የዚህን ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም አሳልፈው በመስጠት ለደርግም ለወያኔም የተመቹትን ሲቃወም በሌላ በኩል ደግሞ የኦሮሞ ሕዝብን ኢትዮጵያዊነት ከሚክዱት ጋር መሰረታዊ ልዩነቱን ይዞ ቆይቷል። የኦሮሞ ሕዝብ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አካል ነበር፤ አሁንም ነው። በመሆኑም የኦሮሞ ሕዝብ ብቸኛ መሪ ብለው ድርጅቶች ለራሳቸው የሰጡትን ስያሜ በውስጡ አያሌ ኦሮሞዎች የታገሉና የተሰዉ መሆናቸውን የሚዘክረው ህብረ ብሄራዊው ኢሕአፓ ተቀብሎት አያውቅም - ከዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ጋር ለመተባባር የነበረውና ያለው ፍላጎት እንዳለ ሆኖ። ስለዚህም ኢሕአፓ የኦሮሞ ሕዝባችን ትግል ላይ የሚሸረበው ሴራ ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል የሚጎዳ ነውና አጥብቆ ይቃወማል፤ ያጋልጣል፤ ይታገላል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኦሮሞ ተወላጆች ላይና በሌሎችም ላይ ጭፍን አፈና እያካሄደ መሆኑ የተወገዘና የቀጠለም ነው። የኦነግ አባል፤ ደጋፊ፤ ፀረ ሰላም ወዘተ እየተባሉ የታገቱ ኦሮሞ ወጣቶች አያሌ ናቸው። አፈናው አልበረደም። ይህ በዚህ እያለ ዛሬ ወያኔ ከተወሰኑት ጋር እደራደራለሁ ብሎ የታጋዩን ጎራ ክፍፍል ለራሱ መጠቀሚያ ለማድረግ መነሳቱ የሚወገዝ ሲሆን በዚህ ተልዕኮው የሚያጅቡት ደግሞ የጥፋቱ ተካፋይ መሆናቸውና በሕዝብም የሚጠየቁ መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል። ራሳቸውን የሽማግሌዎች ወይም አስታራቂ ኮሚቴ ብለው የተሰየሙት ግለሰቦች ተልዕኮና ሚና ወያኔን የሚጠቅም መሆኑን ኢሕአፓ ደግሞ ደጋግሞ ያጋለጠ መሆኑ ሲታወስ በዚህም ያላቸው ሚና ትግልን አደናቃፊ ዳግማዊ ኦሕዴድን ፈጣሪ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ዛሬ ለኦሮሞ ሕዝብ በህቅ ቆሚያለሁ የሚል ሁሉ ከታጋይ ኢትዮጵያውያን ጋር በማበር ፀረ ወያኔ ትግሉን ማፋፋም አለበት እንጂ ከዘረኛው ወያኔ ጋር ከሕዝብ ጀርባ ተመሳጥሮ ለዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዕድሜን በመለገስ የ1983-ኡን ስህተት መድገም አይገባውም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ፀረ ወያኔ ትግል ይፋፋም!!
የአፍራሽ ኃይሎች ሴራ ይከሽፋል!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት የፀና ነው!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France